የሰ/መ/ቁ. 49502

ህዳር 01 ቀን 2003 ዓ.ም

*ዳኞች፣* ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

*አመልካች፣* የኢት/ያ የእህል ንግድ ድርጅት አልቀረቡም

*ተጠሪዎች፣* 1ኛ. መርዕድ ተፈራ

2ኛ አያሌው መኮንን ቀረቡ

3ኛ ስለሺ ኃ/ሚካኤል ቀረቡ

4ኛ ወ/ሪት ዙልፋ ከድር አልቀረበችም

5ኛ አቶ ጣሰው ነገዎ ቀረቡ

6ኛ አቶ አሰፋ ቱሉ ጠበቃ አቶ ወንድአወክ አየለ ቀረበ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የአሁን አመልካች ከተራ ቁጥር 1 እስከ 6ኛ የተጠቀሱት ሠራተኞቹ በሥራቸው ምክንያት የብር 154,334.67/100 የገንዘብ ጉድለት አድርሶውብኛል በማለት እያንዳንዱ ሠራተኛ ኃላፊ ሊሆን ይገባዋል የሚልበትን ምክንያት በመጥቀስ ገንዘቡን እንዲተኩለት ባቀረበው ክስ መነሻ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ተመልክቻለሁ በማለት ተጠሪዎች ኃላፊ ሊሆኑ የሚገባበት ምክንያትና ማስረጃ አልተገኘም በማለት በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ቅር ተሰኝቶ የይግባኝ አቤቱታውን ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነትን አላገኘም፡፡

አመልካች የጉዳዩ አካሄድ እንደ ሙግት አመራር ሥርዓቱ ባለመከናወኑ ምክንያት ተገቢውን ዳኝነት አላገኘም የሚለውን የመከራከሪያ ነጥብ በዋነኛነት በመጥቀስ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪዎችም በሥር የተሰጠው ውሣኔ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም የሚሉበትን ምክንያት ከመግለፅ ጋር ውሣኔው እንዲፀናላቸው ተከራክረዋል፡፡

እኛም ጉዳዩን ተመልክተናል እንደተመለከትነውም የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት ከቀረበው የኦዲት ምርመራ ውጤት በተጨማሪ የኦዲት ምርመራ ሥራውን ያከናወኑት ባለሙያዎች ሙያዊ የምስክርነት ቃል እንዲሰጡለት በማስረጃነት የቆጠራቸው

መሆኑንና ነገር ግን እነዚህ የሰው ማስረጃዎች ሳይሰሙ ታልፎ ውሣኔ በመስጠቱ ፍትህ እንደተጓደለበት ገልፆ ቅሬታ ሲያቀርብ፤

በተጠሪዎች በኩል በሰበር ከቀረበው ክርክር መካከል እነዚህ ኦዲተሮች ከኦዲት ምርመራ ሰነዱ በተለዩ ምን ሊያስረዱ ይቻላሉ? አንደኛውም ኦዲተር ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል ለመስማት የሚቻልበት መንገድ የለም በማለት ከመከራከራቸው ጋር ተገናዝቦ ሲታይ በእርግጥም የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን ማስረጃዎች በሙሉ አለመሰማቱን አረጋጋጭ ነው፡፡

አመልካች በሰው ማስረጃነት የሙያ ምስክርነት እንዲሰጡለት የጠቀሳቸው ኦዲተሮች ሳይሰሙ የታለፈበት ምክንያት ምን እንደሆነ በውሣኔው ላይ ተገልፆ ባይገኝም ከላይ እንደተመለከተው የምስክርነት ቃል አለመስጠታቸውን ከውሣኔው ይዘት መረዳት ችለናል፡፡

እነዚህ የሙያ ምስክሮች የሚሰጡት የምስክርነት ቃል ጉዳዩን በማስረዳት ረገድ የሚኖረው የማስረዳት ብቃትም ሆነ አግባብነት ቃላቸውን ከሰጡ በኃላ የሚታወቅ በመሆኑ ተጠሪዎች በሰበር ደረጃ ባቀረቡት ክርክር እንደገለፁት የኦዲት ምርመራ ውጤቱን ከያዘው ሰነድ የተለየ አያስረዱም ብሎ ከወዲሁ መደምደም የማይቻል ከመሆኑም በላይ አንድ ተከራካሪ ወገን ያቀረበውን ክርክር ለማስረዳት የማስረጃ አግባብነትና ተቀባይነት መርህ ካለገደው ወይም ካልከለከለው በቀር ዘርዝሮ ያቀረበውን የማስረጃ በዓይነትም ሆነ መጠን የማስረዳት መብት ያለው በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት የእነዚህን ምስክሮች የሙያ ምስክርነት ቃል ሳይቀበል በዝምታ አልፎ ውሣኔ መስጠቱ የሙግት አካሄድ ሥርዓትን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም እንዲሁም ጉድለቱ በጥፋት ወይም በቸልተኝነት የተፈፀመ መሆኑን ለማስረዳት የግምት መነሻ ይሆናል የተባለውና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 ከፖሊስ ኮሚሽን የቀረበ የተባለው በቁጥር 272179 የተሰየመው ሰነድ ቀርቦ ስለመታየቱም ሆነ ታይቶ ተቀባይነትን አጥቶ ስለመሆኑ የውሣኔው ይዘት የሚያስረዳው ነገር እንዳሌለ ተረድተናል ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ከውሣኔ ለመድረስ አመልካች ያቀረበውን ክርክር በማስረጃ የማስረዳት መብቱን ሙሉ በሙሉ ጠብቆ ያከናወነ ስለመሆኑ የውሣኔው ይዘትም ሆነ በሰበር ግራቀኙ ያደረጉት ክርክር ስለማያስረዳ የጉዳዩ አካሄድ ሙሉ የክርክር አመራር ሥርዓትን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 01217 በ10/11/2000 እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 72047 በሐምሌ 07 ቀን 2001 የሰጠው ዳኝነት ተሸሯል፡፡

2. የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 01217 የተመዘገበውን መዝገብ እንደገና አንቀሳቅሶ በአመልካች በኩል ማመልከቻው ላይ የጠቀሰውን ጉዳይ ለማስረዳት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 223 መሠረት አስቀድሞ ዘርዝሮ ያቀረበውን ማስረጃ በሙሉ ሰምቶና አይቶ በጉዳዩ ላይ የመሰለውን እንዲወስን መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሠረት መልሰናል፡፡
3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ግራቀኙ ያደረጉት ክርክር ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ሁለቱም ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡን ዘግተናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ም.አ